# የፍትሃዊ ችሎት ብሮሸር
# (Fair Hearing Brochure)

የ Washington ግዛት
Supplemental Nutrition Program (ተጨማሪ የአመጋገብ መርሃ ግብር)
For Women, Infants and Children (WIC፣ ሴቶች፣ ጨቅላ ህጻናት እና ልጆች)

Washington WIC Program

DOH 962-105 November 2023 Amharic

# ፍትሃዊ ችሎት ምንድን ነው?

ፍትሃዊ ችሎት ህጋዊ ችሎት ነው። በፍትሃዊ ችሎት ላይ ታሪክዎን ለዳኛው ይነግራሉ። ዳኛው ከ Women, Infants and Children (WIC፣ ሴቶች፣ ጨቅላ ህጻናት እና ልጆች) መርሃ ግብር አይደሉም። ዳኛው የ WIC መርሃ ግብር እርስዎን በፍትሃዊነት እንዳስተናገድዎት ይወስናሉ።

## ፍትሃዊ ችሎት ለመጠየቅ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

የሚከተሉት ከተከሰቱ ፍትሃዊ የ WIC ችሎት መጠየቅ ይችላሉ:-

- በማንኛውም ምክንያት ለመርሃ ግብሩ ብቁ እንዳልሆኑ ከተነገርዎት እና ይህ ስህተት ነው ብለው ካሰቡ።
- ከመርሃ ግብሩ እያስወጣዎት ከሆነ እና ይህ ኢፍትሃዊ ነው ብለው ካሰቡ።
- ለመርሃ ግብሩ ገንዘብ መልሰው እንዲከፍሉ እየጠየቅዎት ከሆነ።

## ለፍትሃዊ ችሎት እንዴት መጠየቅ እችላለሁ?

የፍትሃዊ ችሎት መጠየቂያ ቅጽ በመሙላት ወይም ደብዳቤ በመጻፍ ወደ እዚህ አድራሻ ይላኩት:-

> Department of Health
> Adjudicative Service Unit
> P. O. Box 47879
> Olympia, WA 98504-7879

በደብዳቤው ላይ ስምዎን፣ አድራሻዎን፣ የ WIC ክሊኒኩን ስም እና ፍትሃዊ ችሎት የፈለጉበትን ምክንያት መጥቀስ ይኖርብዎታል። እባክዎ አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎት ከሆነ ይንገሩን።

## ፍትሃዊ ችሎትን ለመጠየቅ የጊዜ ገደብ አለው?

**አዎ።** ለ WIC ብቁ አይደሉም፣ ከመርሃ ግብሩ አስወጥተንዎታል፣ ወይም ለመርሃ ግብሩ ገንዘብ መልሰው መክፈል አለብዎት በማለት የሚገልጸው ደብዳቤ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለፍትሃዊ ችሎት 60 ቀናት አልዎት።

## የ WIC የምግብ ጥቅማጥቅሞችን ማግኘቴን እቀጥላለሁ?

ለ WIC ብቁ በሆናችሁበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ካሉ እና ከWIC መርሃ ግብር እየተወሰዱ እንደሆነ የሚገልጽ ደብዳቤ ከተጻፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ፍትሃዊ ችሎት ከጠየቁ የWIC የምግብ ጥቅማ ጥቅሞችን **ሊያገኙ <u>ይችላሉ</u>**።

ብቁ የሚሆንበት ጊዜ ካለቀ የምግብ ጥቅማ ጥቅሞችን **አያገኙም**።

ከ WIC መርሃ ግብር እየተወሰዱ ነው የሚለው ደብዳቤ ከተጻፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ፍትሃዊ ችሎት ካልጠየቁ የምግብ ጥቅማ ጥቅሞች **አያገኙም**።

## ፍትሃዊ ችሎት ብጠይቅ መብቴ ምንድን ነው?

- ችሎቱ የፍትሃዊ ችሎት ጥያቄዎ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት 21 ቀናት ውስጥ መደረግ አለበት።
- የችሎቱ ማስታወቂያ ቢያንስ ችሎቱ ከ10 ቀናት በፊት ወደ እርስዎ መምጣት አለበት።
- ችሎቱ እርስዎ በሚኖሩበት አካባቢ ቅርብ መሆን አለበት።
- የህግ ድጋፍን ጨምሮ እርስዎን ለመርዳት ሌሎች ሰዎችን ይዘው መምጣት ይችላሉ።
- እርስዎ እና እርስዎን የሚረዱዎት የWIC መርሃ ግብር በችሎቱ ላይ የሚያቀርባቸውን መዝገቦች ሊመለከቱ ይችላሉ።

### ወደ ፍትህ ችሎት መሄድ ካልቻልኩስ?

ወደ ችሎቱ መሄድ ካልቻሉ ለችሎቱ ዳኛ አስቀድመው ማሳወቅ አለብዎት። አዲስ የችሎት ቀን ይዘጋጃል።

### በፍትሃዊ ችሎት ምን ይሆናል?

- ዳኛው ፍትሃዊ ችሎት ይመራል።
- ዳኛው እርስዎ እና የWIC ሰራተኞች የምትናገሩትን ያዳምጣል። ዳኛው በፍትሃዊነት መያዙን ያረጋግጣል።
- ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መረጃን፣ ምስክሮችን ወይም ሌሎች ማስረጃዎችን ማቅረብ ይችላሉ።
- እርስዎ ወይም ልጅዎ ለምን WIC ብቁ መሆን አለብን ብለው እንደሚያስቡ፣ ለምን በመርሃ ግብሩ ላይ መቆየት እንደሚችሉ፣ ወይም ለምን ለመርሃ ግብሩ ገንዘብ መልሰው መክፈል እንደሌለብዎት ማስረዳት ይችላሉ።
- ዳኛው ለWIC ብቁ መሆን አለቦት ወይም በመርሃ ግብሩ ላይ ለመቆየት መቻል ወይም ለ WIC መርሃ ግብር ገንዘብ መመለስ ካለብዎት በማስረጃው መሰረት ይወስናል።
- ዳኛው ችሎቱን ከጠየቁበት ጊዜ አንስቶ ባሉት 45 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ውሳኔ መስጠት አለባቸው። የዳኛውን ውሳኔ ደብዳቤ በፖስታ ይደርሰዎታል። የውሳኔው ደብዳቤ ለግምገማ አቤቱታ የሚባል ማስታወቂያ ያካትታል።

### በዳኛው ውሳኔ ካልተስማማሁስ?

ውሳኔውን እንዲመረምር የ Department of Health (የጤና መምሪያ) ፀሐፊን መጠየቅ ይችላሉ።

በውሳኔው ይግባኝ ለማለት፣ ለግምገማ አቤቱታውን ሞልተው ወደ Department of Health፣ Adjudicative Service Unit ይላኩ። የውሳኔው ደብዳቤ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ይህን ማድረግ አለቦት።

የ Department of Health ፀሐፊ ውሳኔውን ሊለውጥ የሚችለው:-

- በህጉ ውስጥ ስህተቶች ካሉ
- ችሎቱ በትክክል ካልተካሄደ
- ዳኛው ግልጽ መመሪያ ካልሰጠ
- ለውሳኔው በቂ ማስረጃ ካልተገኘ

የጸሐፊውን ውሳኔ ፍርድ ቤት እንዲመለከት መብት አልዎት። የጸሐፊው የጽሑፍ ውሳኔ የፍርድ ቤት ግምገማ እንዴት እንደሚጠየቅ መመሪያዎችን ያካትታል።

**ስለ ፍትሃዊ ችሎቶች ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካሎት በአካባቢዎ የሚገኘውን የWIC ክሊኒክ ወይም የስቴቱ WIC ቢሮ ይደውሉ። የግዛቱ መሥሪያ ቤት ነፃ የስልክ ቁጥር 1-800-841-1410 ነው።**

የፍትሃዊ ችሎት ሂደቶች በ Federal WIC Program Regulations (የፌዴራል WIC መርሃ ግብር ደንቦች) ክፍል 7CFR 246.9 እና በ Washington Administrative Code (የዋሽንግተን የአስተዳደር ኮድ) 246-10 እና 246-08-520 ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

**የመከላከያ እና የማህበረሰብ ጤና ክፍል**
**Washington WIC**

**WIC መድልዎ አያደርግም።**

ከፌደራል የሲቪል መብቶች ሕግ እና የዩናይትድ ስቴትስ የእርሻ መምሪያ [U.S. Department of Agriculture (USDA)] የሲቪል መብቶች ደንቦች እና ፖሊሲዎች ጋር በተያያዘ፣ ይሄ ተቋም በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በትውልድ አገር፣ በጾታ (በጾታ ማንነት እና በወሲብ አዝማሚያ ጨምሮ)፣ በአካለስንኩልነት፣ በዕድሜ መሰረት አድሎ እንዳያደርጉ ወይም ከዚህ ቀደም ለተሳተፉበት የሲቪል መብቶች እንቅስቃሴ የተነሳ የበቀል ወይም የአፀፋ እርምጃ እንዳያከናውኑ ይከለክላል።

የፕሮግራሙ መረጃዎች ከእንግሊዘኛ ቋንቋ በተጨማሪ በሌሎች ቋንቋዎች እንዲሰጡ ይደረጋሉ። የፕሮግራሙን መረጃ ለማግኘት የተለየ የመግባቢያ ዘዴ የሚያስፈልጋቸው አካለ ስንኩላን ሰዎች (ለምሳሌ እንደ ብሬል፣ በትልቅ ፊደል ሕትመት፣ የድምጽ ቅጂዎች፣ የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ)፣ ፕሮግራሙን የሚያስተዳድሩ የግዛት ወይም የአካባቢው ኤንሲዎች ጋር በመሄድ ወይም ደግሞ የ USDA'ን TARGET ማዕከል በ (202) 720-2600 (በድምጽ እና TTY) ደውለው ማግኘት ወይም በፌደራል ሪሌ ሰርቪስ (Federal Relay Service) (800) 877-8339 በኩል USDA ን ደውለው ማግኘት አለባቸው።

በፕሮግራሙ ላይ የተፈጠረ የአድሎ ሁኔታን አቤቱታ ለማቅረብ፣ ቅሬታ አቅራቢዎቹ የ USDA መርህግብር የአድሎ አቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽ የሆነው ቅጽ AD-3027 መሙላት አለባቸው፣ ቅጹ ኦንላይን በዚህ አገናኝ፦ https://www.fns.usda.gov/sites/default/files/resource-files/ad3027-amharic.pdf ፣ ወይም ከማንኛውም የ USDA ቢሮ፣ በ (866) 632-9992 ላይ በመደወል፣ ለ USDA የሚላክምደብዳቤ በመፃፍ ማግኘት ይችላል። ደብዳቤው የአቤቱታ አቅራቢውን ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር፣ እና ተፈጽሟልምየተባለውን የሲቪል መብቶች ጥሰት ሁኔታ እና ቀን፣ ጉዳዩን የሚመለከተውን የሲቪል መብቶች ምክትል ሴክረታሪ[Assistant Secretary for Civil Rights (ASCR)] መጥቀስ፣ ተፈጽሟል የተባለውን የአድሎ አሰራር በቂ በሆነም ሁኔታ በዝርዝር ማስፈር አለበት። የተሞላው የ AD-3027 ቅጽ ወይም ደብዳቤ ለ USDA በሚከተለው አድራሻ መቅረብም አለበት፦

1. **በደብዳቤ፦**
   U.S. Department of Agriculture
   Office of the Assistant Secretary for Civil Rights
   1400 Independence Avenue, SW
   Washington, D.C. 20250-9410; ወይም

2. **ፋክስ፦**
   (833) 256-1665 ወይም (202) 690-7442፤ ወይም
3. **ኢሜይል፦**
   program.intake@usda.gov

ይሄ ተቋም ሁሉንም ደንበኛ በእኩሌታ የሚመለከት ነው።
WIC መድልዎ አያደርግም።

ይህንን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ 1-800-841-1410 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም በ WIC@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።

Washington State Department of HEALTH

WIC WASHINGTON

DOH 962-105 November 2023 Amharic